ድርጅታዊ መግ ለጫ

ኪል_0012/07
ሚያዚያ 8 ቀን፣ 1999 ዓ.ም

# በፈጠራ አሉባልታ የሚዳከም ትግልና የሚፈታ አመራር የለም

የህዘባችን አልገዛም ባይነት ውስጥ ለውስጥ ተጠናክሮ የወያኔን አገዛዝ እያስጨነቀው ባለበት ባሁኑ ወቅት አገዛዙ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን አጥቶ ዕንደ አበደ ዕንስሳ እየተቅበዘበዘ ይታያል።

ከሰሜን እስከ ደቡብ ፣ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በመሳሪያ ሃይል አፍኖ ለመግዛት ያደረገው ሙከራ እንደ አሰበው አልተሳካለትም። ባገር ውስጥ ያለውን ያፈና አካሄድ ሊሸፍንልኝ ይችላል ብሎ ባሰበው የዓለም ዓቀፍ ሽብርተኝነት ተፋላሚ ተዋናይነት የከሰረ ሥሌት የኢትዮጵያን ውድ ልጆች በባዕድ አገር ልኮ በውክልና ጦርነት ደም ከማስፈሰስ፣ የድህነት ሀብቷን ከማሚጠጥ በስተቀር የተፈለገውን ድል ላሳዳሪዎቹ፣ ላገዛዙ ደግሞ ከበሬታን ሊፈጥርለት አልቻለም።

ይህ በቅጥፈትና በፈጠራ ወሬ ራሱን ዋሽቶ የኢትዮጵያን ሕዝብና ዓለም ዓቀፉን ሕብረተሰብ ደጋግሞ በመዋሸት ፖለቲካ መሥራት ይቻላል ብሎ እራሱን አሳምኖ በጥፋት ፈረሱ እየጋለበ ያለ አገዛዝ ወደ ታሪካዊ ፍጻሜው እየተቃረበ ያለ ይመስላል።

በፈጠራ ክስና በሀሰት ምስክር ብርቅዬ መሪዎቻችንን፣ ባስርተ ሺዎች የሚቆጠሩ አባላትንና ደጋፊዎችን የከሰሰ ያሰረና ያሥበየነ፤
ለተሰረቀ የህዝብ ድምጽ መከበር ባዶ እጃቸውን በጠራራ ጸሐይ ባጋዚ ጦር አስጨፍጭፎ በባንክ ዘረፋ የወነጀለ፣
በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከሚኖሩበት አገር የሚያሶጣ ሰነድ ሣያገኙ አስመራ ሄደው ከሻቢያ ጋር አገዛዜን ለመገልበጥ ተደራደሩ፣
አገዛዙ ሰባ ሚሊዮን የኢትዮጵያን ህዝብ በሽብር እየረገጠና እየገዛ ለመብቶች መከበር የሚታገሉትን በሽብርተኛነት መክሰስ የሚቀናው ይሉኝታ ቢስ አገዛዝ ነው።

ከላይ የጠቀስናቸውን የአስተዳደር ብልሽቶች እንደ ዴሞክራሲያዊ ድል እየቆጠሩ ሙያዊ ሃላፊነትን በማይሰማቸው ያገዛዙ ገደለ ማሚቶዎችና ለሚጣልላቸው ቁራሽ ዳቦ ያደሩ የዜና ማሰራጫዎች የበሬ ወለደ የፈጠራ ታሪካቸውን በመዘገብ የማደናቆር ተልዕኮአቸውን በስፋት ቀጥለዋል።
ከወያኔ የፈጠራ ውሸት መፈብረኪያ መድረኮች አንዱ በሆነው አይጋ ፎረም( Aiga Forum) ቅንጅት ዓለም ዓቀፍ ለቃሊቲ መሪዎቹ የላከው ተብሎ የተሰራጨው ደብዳቤ በድረ ገጹ አሰራጭቷል።

ይህ የፈጠራ ስራ የህዝብ ወገኖችን ብዙ ግራ ያጋባል ብለን ባናምንም በጎደሉ የአመራር አባላትን የመሙላትና የተጣለብንን ድርጅታዊ ኃላፊነት ለመወጣት በምናደርገው ዝግጅት ላይ የሚፈጥረው እንቅፋት አይኖርም። ለውንጀላና ለመከፋፈል ይረዳኛል ብሎ ባሰበው መንገድ አቀናብሮ ቢያቀርበውም ለእንቅስቃሴአችን ተጠናክሮ መቀጠል እንቅፋት ለመፍጠር ግን የማይችል መሆኑን በተግባር እናረጋግጣለን።

የቅንጅት ዓለም ዓቀፍ አመራር በሰው ሃይል ማጠናከር አሰፈላጊነት በአይጋ ፎረም ተጠልፎ የሚሰናከል አይሆንም። ለዴሞክራሲያዊው ትግል መጠንከር ወሳኙ ያመራራችን በሰው ሃይል መጠናከር መሆኑን ስለምናምን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ አሟልተን ለመቀጠል የሚያግደን ምንም ሃይል እንደሌለ እየገለጽን አይጋ ፎረም እንደገድል የቆጠረውና በፈጠራ ያቀናበረው ሪፖርት ከወሬነት አልፎ የተመኘውን ሽብር እንደማይፈጥርለት አበክረን እንገልጻለን።

**የቅንጅት አለም አቅፍ የፖለቲካ አመራር**